# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት

## በዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ጀሰ-ሀሪንግ የተላለፈ ትዕዛዝ
## (በ11/21/21 የተሻሻለው)

በማርች 18፣ 2020 በተላለፈውና በመይ 29፣ 2020 ዳግም በተረጋገጠው ትዕዛዝ መሰረት፣ ጆይንት ኮሚቲ ኦን ጁዲሽያል አድሚኒስትሬሽን (የፍትህ አስተዳደር የጋራ ኮሚቴ) አሁን ባለው የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜና ለፍትህ አስተዳደርም የተሻለ ስለሆነ፣ በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ታግደው፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆመው (ቶል ተደርገው) እና ተራዝመው የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችሉ ትዕዛዞች የማስተላለፍ ስልጣን ለዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ሰጥቷል።

በማርች 18፣ 2020፣ በማርች 19፣ 2020፣ በመይ 14፣ 2020፣ በጁን 19፣ 2020፣ በኦገስት 13፣ 2020፣ በኖቬምበር 5፣ 2020፣ በጃንዋሪ 13፣ 2021፣ በማርች 30፣ 2021፣ በመይ 12፣ 2021፣ በጁላይ 14፣ 2021 እና በሰፕተምበር 11፣ 2021 በተላለፉት ትዕዛዞች፣ ዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) እንደሚከተለው አዝዞ ነበር፡ (በግልጽ ካልተጠቀሰ በስተቀር) ሁሉም ከኖቬምበር 21፣ 2021 በፊት እንዲፈጸሙ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች፣ የአሁኑ የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ (ጁዲሽያል ኢመርጀንሲ) በስራ ላይ እስካለ ድረስ ይታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆሙ (ቶል ይደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘሙ ዘንድ ታዟል። በትዕዛዙ እንደተመለከተው፣ የጊዜ ገደቦቹ፣ ሁኔታዎች ሲቀየሩ ለተጨማሪ ጊዜ ሊታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ሊቆሙ (ቶል ሊደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ሊራዘሙ ይችላሉ። እገዳው፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆሙ (ቶል መደረጉ)፣ እና መራዘሙ በዚህ ትዕዛዝ ካልሰፈረ በስተቀር ቢያንስ እስከ አርብ፣ ኤፕሪል 8፣ 2021 ድረስ ይቀጥላል።

ፍርድ ቤቱ እስከ አርብ፣ ኤፕሪል 8፣ 2021 ድረስ የሚሰማቸው የመዝገቦች አይነቶችና ብዛት በማስፋት ይገኛል።

ከታች ከተለዩት የመዝገብ አይነቶች በስተቀር፣ ሁሉም እስከ አርብ፣ ኤፕሪል 8፣ 2021 ድረስ ተቀጥረው የነበሩ ቅድሚያ-የማይሰጣቸው (ናን-ፕራዮሪቲ) መዝገቦች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል፣ አዲስ ቀን ቀጠሮ ይያዝላቸዋል፣ አስቸኳይ የሆኑ መዝገቦች ተይዞላቸው ባለ የፍርድ ቤት ቀን ቀጠሮ ይቀጥላሉ፣ ከታች እንደተቀመጠውም ይሰማሉ።

የኮቪድ-19 ምልክቶች ያለባቸው፣ ጠበቆችም ይሁኑ ሌሎች ሰዎች፣ ወደ ፍርድ ቤት ክፍል በአካል መምጣት የለባቸውም። https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/about/symptoms.html ይመልከቱ።

ሁሉም ወደ ሱፐርየር ፍርድቤት የሚገቡ ሰዎች አፍንጫቸውና አፋቸው የሚሸፍን ጭንብል ማድረግ ይኖርባቸዋል። Order Requiring Persons To Wear Cloth Face Coverings In Court Buildings During The Covid-19 Pandemic (በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጊዜ በፍርድ ቤት ህንጻዎች የሚገቡ ሰዎች በልብስ የተሰራ የፊት መሸፈኛ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ትእዛዝ) ይመልከቱ።

ፋይል ለሚደረጉ ማመልከቻዎች (ፐሊዲንግስ)፣ አቤቱታዎችና አዳዲስ መዝገቦች ለመቀበል፣ ሁሉም ክፍሎችና (ዲቪዥንስ) የቤተሰብ ፍርድ ቤት በርቀት (ሪሞትሊ) እና በአካል ክፍት ይሆናሉ። በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረጉ ይቀጥላል። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለርክ'ስ ኦፊስስ) የርቀት ክወናዎች (ሪሞት ኦፐሬሽንስ) ማስታወቂያዎችን ይመልከቱ። http://www.dccourts.gov/coronavirus

ፍርድ ቤቱ በዚህ ወቅት በተወሰኑ ሁኔታዎች ክፍያዎች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በመቀበል ይገኛል። ለበለጠ ዝርዝር መረጃ https://www.dccourts.gov/services/online-payment ይመልከቱ።

በሕግ እስከ ተፈቀደ ድረስ፣ በርቀት የሚደረጉ ችሎቶች ለማህበረሰብ አባላት ቀጥተኛ ተደራሽነት ይኖራቸዋል። በርቀት በሚደረጉ የፍርድ ቤት ችሎቶች በቀጥታ እንዴት መስማት/መከታተል እንደሚቻል ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ተለጥፏል። https://www.dccourts.gov/services/remote-hearing-information

ከጁላይ 12፣ 2021 ጀምሮ በሁሉም ክፍሎች (ዲቪዥንስ) ያሉ ሁሉም የሱፐርየር ፍርድ ቤት ጸሀፊ (ክለክስ ኦፊስ) መኮንኖች (ኦፊሰርስ)ክፍት ናቸው።

ፍርድ ቤቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች በዋናነት በርቀት (ፕራይመርሊ ሪሞትሊ) ይሰራል፡

**<u>የፍትሐ ብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)</u>**

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በህጎች (ክስ የሚቀርብባቸው የጊዜ ገደቦችም (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽን) ጭምር)፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች፣ የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ባለበት ጊዜ አይታገዱም፣ ከተፈጻሚነት

ለጊዜው አይቆሙም (ቶል አይደረጉም)፣ እንዲሁም ደግሞ አይራዘሙም። እንዲህ የማይሆንባቸው የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች አሉ፡ (1) በማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ህጋዊ ክልከላ (ስታቹቶሪ ሞራቶርየም) የሚመለከታቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ክስ የሚቀርብባቸው የጊዜ ገደቦች (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽን) ክልከላው እስኪያበቃ ድረስ ይታገዳሉ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም፣ እና (2) በሱፒርየር ፍርድ ቤት የአከራይና-ተከራይ ቅርንጫፍ የስነ ስርአት ደንቦች (ሩልስ ኦፍ ፕሮሲጀር) ደንቦች (ሩልስ) 16(a)(4) እና 16(c) መሰረት ከመኖሪያ ቤት ማስወጫያ ትዕዛዝ (ሪትስ ኦፍ ረስቲቱሽን) ትክክለኛነት እና መስጠት የተመለከቱ በአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎታቸው ያበቃ የነበረ የጊዜ ገደቦች ይህ ትእዛዝ ከወጣበት ቀን በኋላ እስካሉ 14 ቀናድ ድረስ ይታገዳሉ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም።

የፍትሐ ብሔር ክፍል በሚከተለው መልኩ ይሰራል፡

- በጁሪ ከሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) በስተቀር ችሎቶች በርቀት መካሄድ ይቀጥላሉ።

- ዳኞች በምናባዊ (ቨርቹዋል) የፍርድ ቤት ክፍሎች ችሎቶች በሳምንት ለአምስት ቀናት ያህል በርቀት ያካሂዳሉ። በጁሪ ከሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) በስተቀር፣ በአካል እንዲቀርቡ በዳኛው ካልታዘዙ በስተቀር ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ጠበቆች በአካል መቅረብ የለባቸውም።
- የፍትሐ ብሔር ክፍል በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) ዳግም መስማት ጀምሯል። የፍትሐ ብሔር ክፍል ቢያንስ ሶስት በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች በአንድ ጊዜ የማካሄድ ችሎታ አለው። ለጤናና ደህነንት ምክኒያቶች ሲባል ታዛቢዎች በጁሪ-የሚዳኙ የፍትሐ ብሔር ክርክሮችን በርቀት እንዲከታተሉ ይበረታታሉ፣ ፍርድ ቤቱም በፍርድ ቤት ክፍል በአካል የሚገኑትን ሰዎች ቁጥር የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።
- የፍትሐ ብሔር ክፍል በበርካታ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት የሚካሄዱ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች ማካሂዱን ይቀጥላል።

- የፍትሐ ብሔር ክፍል በፍርድ ቤት በአካል የሚካሄዱ በጁሪ-የሚዳኙ ወይም በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች ቀነ ቀጠሮ ሲመድብ፣ ክርክር የሚደረግበት ቀነ ቀጠሮው የሚመድበው ሁሉም ጠበቆች ወይም ተከራካሪ ወገኖች በተገኙበት ችሎት ነው።

- የፍትሐ ብሔር ክፍል፣ ማስረጃ የሚሰማባቸው ችሎቶች (ኤቪደንሻሪ ሂሪንግስ) እና ዳኛ የሚዳኛቸው ክርክሮች (ቤንች ትራያልስ) ጨምሮ፣ በማንኛውም ተገቢ በሚሆንበት ሁኔታ ችሎቶች በርቀት ማከናወኑ ይቀጥላል።

- ማናቸውም የአስቸኳይ ማመልከቻ (ኢመርጀንሲ ሞሽን) ወደ Civilefilings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

- የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻዎች (አፕሊኬሽን ፎር ፊ ወይቨርስ) እና ማናቸውም ከማመልከቻው ጋር ፋይል የሚደረግ ወደ Civilefilings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

- በሞልትርየ ፍርድ ቤት ክፍል የሚገኝ የፍትሐ ብሔር እርምጃዎች ቅርንጫፍ (ሲቪል አክሽንስ ብራንች) እና በህንጻ B የሚገኙ የአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎችና የአከራይና-ተከራይ ቅርንጫፎች ጸሀፊ ቢሮዎች (ክለርክስ' ኦፊስስ) ያሉ የህዝብ መስኮቶች (ፓብሊክ ዊንዶውስ) ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 - 5፡00 ክፍት ናቸው። የጸሀፊ ቢሮ የህዝብና ሰራተኞች ጤና ለመከላከል ማህበራዊ ርቀትንና የብዛት ገደቦች ይጠቀማል። የተወሰኑ ሰራተኞች በአካል የሚሰሩ ሲሆን ሌሎኞቹ ሰራተኞች በርቀት ስራቸውን ማከናወን ይቀጥላሉ።

- ፋይል አድራጊዎች በአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎችና በአከራይ-ተከራይ መዝገቦች ማህተም አስመትተው ጥለው ይሄዱ ዘንድ የመጣያ ሳጥኖች (ድሮፕ ባክስስ) በህንጻ B ተገጥመዋል።

- ሁሉም ከኪራይ ቤት የማስወጣቶች (ኢቪክሽንስ)፣ የመኖሪያ ቤት ሀራጅ (ፎርክሎዠር) የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ እና የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ ህግ እስከሚፈቅደው ድረስ ተግባራዊ ሳይሆኑ ይቆያሉ። ነገር ግን፣ እንደነዚህ የመሳሰሉ ህጋዊ ገደቦች ከተነሱ፣ ገደቡ ከተነሳ በኋላ በተሰጣቸው ቀነ ቀጠሮ መሰረት ይቀጥላሉ።

- የፍትሐ ብሔር ክፍል ተፈጻሚነታቸው ባልታገደ የኪራይ ቤት ማስወጣቶች (ኢቪክሽን)፣ መኖሪያ ቤት ሀራጅ (ፎርክሎዠር)፣ እና የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) መዝገቦች የርቀት ችሎቶች ወይም በደረሱ ማመልከቻዎች ውሳኔ (ሩል ኦን ራይፕ ሞሽንስ) ያካሂዳል።

- ፍርድ ቤቱ በመከላከያ ትዕዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) በሚያዘው መሰረት በአካል የሚደረጉ ክፍያዎች መቀበል ይችላል። ተከራዮች ***በጥሬ-ገንዘብ ያልሆነ*** ክፍያን ከሚከተሉት ዘዴዎች አንዱን በመጠቀም መክፈል ይችላሉ፡ (1) ክፍያዎን ወደ አከራይና-ተከራይ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በአካል በማምጣት ወይም በፖስታ በመላክ፡

Landlord and Tenant Clerk's Office, 510 4th Street NW, Room 110, Washington, DC 20001፣ (2) ክፍያዎን በህንጻ Building B፣ 510 4th Street NW, Washington, DC 20001 አድራሻ በሚገኘው መጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በማስገባት፣ የመዝገብ ቁጥሩ (ኬዝ ናምበር) በክፍያው መጻፍ አለበት፣ (3) ክፍያዎን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በፍርድ ቤቱ ፖርታል በኩል። ይህ የሚሆነው የወር ጠቅላላ ክፍያው ከ$1,000 የማይበልጥ ሲሆን ነው። እባክዎ ክፍያዎችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መፈጸም እንደሚችሉ የወጣውን የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለርክ'ስ ኦፊስስ) አሰራር ማስታወቂያን ይመልከቱ፡ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Superior-Court-Clerks-Offices-Remote-Operations.pdf። ***በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች*** ፍርድ ቤቱ በውሱን ሁኔታዎች ሊቀበል ይችላል። ቀናትንና ሰአታትን በተመለከተ እባክዎ የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለርክ'ስ ኦፊስስ) ማስታወቂያን ይመልከቱ (ከላይ ያለውን ማስፈንጠሪያ (ሊንክ) ይጫኑ)። ተከራይ የመከላከያ ትዕዛዙን ማሻሻያ ካላገኘና ክፍያውን ወደ ፍርድ ቤት ሬጂስትሪ ወይም በአስቸኳይ ጊዜ በቀጥታ ለአከራይ ካልፈጸመ፣ እና አከራዩ በመቀጠል ማእቀቦች (ሳንክሽንስ) ይጣሉ ዘንድ ከጠየቀ፣ ፍርድ ቤቱ ከሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎች በተጨማሪ የህብረተሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታ ጋር የተያያዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል።

- አስተዳደራዊ ትዕዛዝ 06-17 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 06-17) ምን ይበል ምን፣ የመጥሪያ ማድረሻ ቃለ መሀላዎች (አፊዳቪትስ ኦፍ ሰርቪስ) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

- አስተዳደራዊ ትዕዛዝ 15-03 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 15-03) ምን ይበል ምን፣ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ ጥሰቶች መዝገቦችና፣ እንደነ ወሳኝ ኩነት ሰነዶች የማሻሻል ማመልከቻዎች፣ የስም ለውጦች፣ የጾታ ምደባዎች (ጀንደር አሳይመንትስ)፣ የውጭ አገር የፍርድ ቤት መጥሪያ (ፎረይን ሰፒና)፣ የፍትሐ ብሔር የንብረት መውረስ (አሰት ፎርፌይቸር) አቤቱታዎች፣ የመረጃ ስም ማጥፋት (ሊበልስ ኦፍ ኢንፎርሜሽን)፣ እና ጓዳዊ ክሶች (ፍርየንድሊ ሱትስ) ጨምሮ ሁሉም በጀጅ-ኢን-ቻምበርስ የሚሰሙ መዝገቦች በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (CaseFileXpress) በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

- ደንብ 5 እና 5-III የሰፈረው ምን ይሁን ምን፣ ታትመው ያሉ (ሲልድ) መዝገቦችና በመዝገብ ቁጥራቸው SLD የሚል ያለባቸው (ለምሳሌ፡2020 CABSLD 000001)፣ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ሰነዶች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ባልታተመ (አንሲልድ) መዝገብ፣ የታተሙና (ሲልድ) ያልተቀነሰባቸው (አንሪዳክትድ)

ሰነዶች ወደ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በአካል፣ በወረቀት በፖስታ ወይም በመጣያ ሳጥን (ድራፐ ባክስ) በኩል ማስረከቡ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

- በርቀት የሚደረጉትን ችሎቶች ለማቀላጠፍ የፍትሐ ብሔር ክፍል ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለፍትሐ ብሔር ክፍል ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) እንዲሰጡ ያበረታታል። እባክዎ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ ወገንን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ከታች ወዳሉት የኢመይል አድራሻዎች ኢመይል ያድርጉ፣ ወይም ከታች ወደ ተዘረዘሩት የቴሌፎን ቁጥሮች ይደውሉ።

| | | |
|---|---|---|
| የፍትሐ ብሔር እርምጃዎች ቅርንጫፍ | CivilDocket@dcsc.gov | (202) 879-1133 |
| የአከራይና-ተከራይ ቅርንጫፍ | LandlordandTenantDocket@dcsc.gov | (202) 879-4879 |
| የአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ቅርንጫፍ | SmallClaimsDocket@dcsc.gov | (202) 879-1120 |

## የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)

ከማርች 15፣ 2021 ጀምሮ ፍርድ ቤቱ የ90-ቀን የክስ ጊዜ (ኢንዳይክትመንት ታይምላይን) ከተፈጻሚነት ማቆሙ ያቆማል (D.C. Code §23-1322(h))።

ከኤፕሪል 15፣ 2021 ጀምሮ ፍርድ ቤቱ በእስር ያሉ መዝገቦች ብቻ የ9-ወር የክስ ጊዜ (ኢንዳይክትመንት ታይምላይን) ከተፈጻሚነት ማቆሙ ያቆማል (Rule 48 (c)(1), D.C. Code § 23-102)።

ከኤፕሪል 26፣ 2021 ጀምሮ ፍርድ ቤቱ የ100-ቀን የክርክር የጊዜ መስመር (ትራያል ታይምላይን) ከተፈጻሚነት ማቆሙ ያቆማል (D.C. Code §23-1322(h))።

ከማርች 15፣ 2020፣ በ§ D.C. Code 11-947(c) መሰረት ከላይ ያሉትን የጊዜ መስመሮች መጀመሪያ ከተፈጻሚነት ያቆሙት ቀን ያለውን ክፍለ ጊዜ፣ ጀምሮ እስከ ከተፈጻሚነት የሚቆምበት ጊዜ ድረስ ያለው ቀን የክስ እና/ወይም የክርክር የጊዜ ገደቦች ስሌት መካተት የለበትም።

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ ሁሉም ሌሎች የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜው ስራ ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትዕዛዝ

እስከሚሰጥ ድረስ፣ መታገድ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆም (ቶል መደረግ)፣ መራዘም ይቀጥላሉ። ይህ፣ የሚከተሉትና ሌሎችን ያካትታል፡ በደንቦች (ሩልስ)5.1 እና D.C Code § 231322(a) እና (b) መሰረት የተቀመጡ የመጀመሪያ ችሎቶች የጊዜ ሰሌዳዎች (ታይምላይንስ ፎር ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ እንዲሁም ደግሞ የሚከተሉትን ጨምሮ የክስ መመስረቻ የጊዜ ገደቦች (ኢንዳይትመንት ዴድላይንስ) እና የክርክር የጊዜ ገደቦች፣ እና በD.C. Code §§ 23-102, 23-1322(h)፣ 24-801 እና 24-531.01 et. seq. መሰረት የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች።

ከዚህ ቀደም የተላለፉ የሚከተሉት ትዕዛዞች ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ተራዝመዋል፡

- በማርች 16፣ 2020 የተላለፈው የህግ አስከባሪዎች ለተጨማሪ ግለሰቦች በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሳይቴሽን) እንዲፈቱ ፈቃድ የሚሰጥ ትዕዛዝ።
- በማርች 27፣ 2020 የተላለፈው ህግ አስከባሪዎች ለተወሰኑ የቀላል-ወንጀል የዳኛ እስር ትዕዛዝ (ሚስደሚነር ቤንች ዋራንትስ) አይነቶች ቁጥጥር ስር ውስጥ ማስገባቱን ያገደ ትዕዛዝ።
- በማርች 27፣ 2020 የተላለፈው የሳምንት መጨረሻ የእስር ፍርዶች (ዊከኤንድ ጀይል ሰንተንስስ) ያገደ ትዕዛዝ።
- በኤፕሪል 1፣ 2020 የተላለፈው፣ ወደ ጎን ስለ ተተዉ ክሶች (ዲፈርድ ፕሮሰኩሺንስ) እና የፍርድ ስምምነቶች (ሰንተንሲንግ አግሪመንትስ) እና የፕሮቤሽን ዝርዝሮች (ፕሮቤሽናሪ ተርምስ) መዝገቦች እየወደቁ ያሉ ጊዜያትን ሁኔታ በተመለከተ ለማብራራት የወጣው ትዕዛዝ።
  - በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት ከእስር ለመውጣት አስቸኳይ አቤቱታዎች ፋይል ማድረጊያ ስነ ስርአቶች ያቋቋመ ትዕዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)።
  - በኦክቶበር 4፣ 2021 የቀላል ወንጀል የማህበረሰብ ፍርድ ቤት ካላንደሮች የሚያዝ የተሻሻለ ትዕዛዝ (አመንድድ ስታንዲንግ ኦርደር)።
  - በኖቮምበር 8፣ 2021 የከባድ ወንጀል ካላንደሮች የሚያዝ የተሻሻለ ትዕዛዝ (አመንድድ ስታንዲንግ ኦርደር)።

የወንጀለኛ ክፍል እንደሚከተለው ይሰራል፡

ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ የሚከተሉት ካላንደሮች ሙሉ በሙሉ በርቀት ይካሄዳሉ፣ እና ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በተቻለ መጠን በቪድዮ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን፣ መቅረብ ይኖርባቸዋል። በርቀት መቅረብ የማይችሉ ወገኖች ለችሎታቸው በርቀት ለመቅረብ እንዴት መግባት እንደሚችሉ (ሎግ-ኢን ለማድረግ) እርዳታ ያገኙ ዘንድ በፍርድ ቤቱ በሚገኘው የመረጃ ዴስክ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

- ዩ.ኤስ.ኤ./ኦ.ኤ.ጂ. የጥቅስ የእምነት ክህደት እና አቅጣጫ መቀየርያ ካላንደር (ሳይቴሽን አረይንመንት ኤንድ ዳይቨርዥን ካላንደር)
- የአእምሮ ጤና የማህበረሰብ ፍርድ ቤት
- የሱፒርየር ፍርድ ቤት የአደንዛዥ እጽ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (የአደንዛዥ እጽ ፍርድ ቤት)

- የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) እና መቅረቦች (ፕረዘንትመንትስ) በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር C-10 ይሰማሉ። በቪድዮ መቅረቡን የሚቀጥሉት በዲ.ሲ እስር ቤት (ጀይል) ካሉ ተከላካዮች በስተቀር የመንግስትና የተከላካይ ጠበቃና ተከላካይ በአካል በፍርድ ቤቱ ይቀርባሉ። የወደ ሌላ ክልል የሸሸ ወንጀለኛ መዝገቦች (ፉጂቲቭ ማተርስ) ወደ ተከሰሶበት የነበረ ክልል መመለሻ ችሎት (ኤክስትራዲሽን ሂሪንግስ) እስከ ጃንዋሪ 5፣ 2022 በ C-10 መሰማት ይቀጥላሉ፣ ከጃንዋሪ 12፣ 2022 ጀምሮ ወደ ተከሰሶበት የነበረ ክልል መመለሻ ችሎት (ኤክስትራዲሽን ሂሪንግስ) በዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ቀጠሮ ይያዝላቸዋል።

- ሁሉም በእስር-የሌሉና በእስር ያሉ መዝገቦች በተመደበው የቀላል ወንጀል የማህበረሰብ ፍርድ ቤት እና በከባድ ወንጀል ካላንደሮች ይቀጥላሉ፣ እነዚህም በተመደበላቸው ፍርድ ቤቶች በርቀትና በአካል የሚካሄዱ ይሆናል።

- ሁሉም የፍርድ ቤት ክፍሎች፣ የተከላካዮች፣ ምስክሮች፣ ተበዳዮች፣ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጁረሮች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጤናና ደህንነት በሚጠብቅ መልክ በአካልና በርቀት ለማሳተፍ ተዋቅረዋል።

  - **ከእስር ተፈተው ያሉ ተከላካዮች** እስከተቻለ ድረስ በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ፣ ፍርድ ቤቱ በአካል እንዲቀርቡ ካላዘዘ በስተቀር፣ በቴሌፎን መቅረብ ይችላሉ።
  - ለክርክር (ትራያል)፣ እና እስር እና ቅድሚያ ችሎቶች (ዲተንሽን ኤንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) በስተቀር፣ **በዲፓርትመንት ኦፍ ሪሃብሊቴሽን ሰርቪስስ (በተሀድሶ አገልግሎቶች ክፍል)፣ በእስር ቤቶች ቢሮ (ቢሮ ኦፍ ፕሪዝንስ)፣ እና በዲፓርትመንት ኦፍ ቢሄቨየራል ሄልዝ (የባህርይ ጤና ክፍል) ስር ያሉ ተከላካዮች በርቀት መቅረቡን መቀጠል ይችላሉ።**
  - ለክርክር (ትራያል)፣ እና እስር እና ቅድሚያ ችሎቶች (ዲተንሽን ኤንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) በስተቀር፣ **በዲፓርትመንት ኦፍ ኮሬክሽንስ (በማረሚያ**

**ቤት ክፍል) ስር በቀላል ወንጀል መዝገቦች ያሉ ተከላካዮች በርቀት መቅረቡን መቀጠል ይችላሉ።**

- ተከላካይ በችሎት የመቅረብ መብቴን በገዛ ፈቃዴ እተዋለሁ ካላለ በስተቀር **በዲፓርትመንት ኦፍ ኮሬክሽንስ (በማረሚያ ቤት ክፍል) ስር በከባድ ወንጀል መዝገቦች ያሉ ተከላካዮች በአካል ይቀርባሉ።**
- ተከላካይ በርቀት መቅረብ የሚችል ከሆነ፣ **የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆችም** በርቀት በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ።
- ተከላካይ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆችም** በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።
- በግለሰብ መዝገብ በርቀት ምስክርነት እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር በሁሉም ሂደቶች ያሉ **ምስክሮች** በአካል ይቀርባሉ።
- **የቅድመ ክርክር አገልግሎቶች (ፕሪትራያል ሰርቪስስ) እና የፍርድ ቤት አገልግሎቶች እና የበዳይ ክትትል ኤጀንሲ ተወካዮች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።
- **የወንጀል ሰለባዎች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

- የአቅም ገደቦች ታሳቢ ባደረገ መልኩ **የማህበረሰቡ አባላት** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

## <u>የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ፣ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም።

የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) (ዲ.ቪ.ዲ.) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በአካልና በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ድረስ ከሰኞ እስከ አርብ ድረስ ይገኛል።

- በሞልትርየ ህንጻ የሚገኝ የዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) ክፍት ነው።

- የፍትሐ ብሔር ፋይል የሚደረጉ ነገሮች በጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በአካል ወይም በርቀት መደረግ ይችላሉ፡
  1. በበይነ መረብ (ኦንላይን) በwww.probono.net/dccourts፣ ወይም፣
  2. በዲ.ቪ.ዲ. ድረገጽ የሚገኙትን ቅጾች ሞልቶ ወደ DVD@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ። ሊሞሉ የሚችሉ ቅጾች ለማግኘት በሚከተለው ይጫኑ፡ here (ከዚህ)።

- በዲ.ቪ.ኤም. እና በሲ.ሲ.ሲ. መዝገቦች የወንጀለኛ ፋይል የሚደረጉ ነገሮች ኬዝፋይልኤክስፕረስ በመጠቀም በበይነ መረብ (ኦንላይን) ፋይል ማድረጉ መቀጠል ይኖርባቸዋል። እንደየ የመዝገቡ አይነቶች፣ ዳኞችና የፍርድ ቤት ክፍል ሰራተኞች (ኮርትሩም ስታፍ) በአካል ወይም በርቀት ይሰራሉ። በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት በሚካሄዱ ችሎቶች ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎንና በቪድዮኮንፈረንስ መቅረቡን መቀጠል ይችላሉ።

- በዲ.ቪ.ዲ. የሚካሄዱ የፍርድ ቤት ሂደቶች ለህዝብ ክፍት ናቸው። ተከራካሪ ወገኖች ወደ ፍርድ ቤት ክፍሉ እንዴት በቀጥታ መግባት እንደሚችሉ መመርያዎች ያገኛሉ። ተከራካሪ ወገኖች-ያልሆኑ የዲ.ቪ. ክፍል የጸሀፊ ቢሮን በ (202) 879-0157 በመደወል ወይም ወደ DVDhearings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ ወደሚፈልጉት ፍርድ ቤት ክፍል መግቢያ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

- የዲ.ቪ. ክፍል ሰባት በስራ ላይ የሚሆኑ የፍርድ ቤት ክፍሎች ይኖሩታል። ገሚሶቹ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በርቀት የሚሰሩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በአካል የሚሰሩ ይሆናሉ። ከታች ያሉትን የፍርድ ቤት ክፍሎች ዝርዝር በፍርድ ቤቱ ከተመደቡ የችሎቶች አይነቶች ጋር ይመልከቱ፡

  - 113 – የሲ.ፒ.ኦ.፣ ኤ.ኤስ.ኦ. መዝገቦች
  - 114 – የሲ.ፒ.ኦ.፣ ኤ.ኤስ.ኦ. መዝገቦች
  - 117 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. መዝገቦች
  - 118 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. መዝገቦች
  - 119 – መዝገባቸው በማጂስትሬት ዳኛ የሚሰማ ዋና የቲ.ፒ.ኦ.፣

ቲ.ኤ.ኤስ.ኤ. የፍርድ ቤት ክፍሎች

- 108 – መዝገቦቹ በሲንየር (ጥሮተኞች) ዳኛ የሚሰማ ተጠባባቂ የሲ.ፒ.ኤ. የፍርድ ቤት ክፍሎች
- JM-9 – ተጠባባቂ የቲ.ፒ.ኤ.፣ ቲ.ኤ.ኤስ.ኤ. መዝገቦች እና ዋነኛ የልጅ ቀለብ መዝገቦች የፍርድ ቤት ክፍል

<u>የወንጀለኛ መዝገቦች – የቤት ውስጥ ሁከት ቀላል-ወንጀል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሚስደሚነር) (ዲ.ቪ.ኤም.) እና የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ክሪሚናል ኮንተምፕት) (ሲ.ሲ.ሲ.)</u>

- ሁሉም የከእስር የተፈቱ ተከላካዮች ችሎቶች **<u>አይራዘሙም</u>**፣ በተመደበላቸው ቀንና ሰአት በፍርድ ቤት ቁጥር 117 እና በፍርድ ቤት ቁጥር 118 **<u>በርቀት</u>** ይካሄዳሉ። ይህ፣ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ የእምነት ክህደት ቃል የሚሰጥባቸው ችሎቶች (አረይመንት ሂሪንግስ)፣ የዲ.ኤስ.ኤ. ግምገማና ፍርድ የሚሰጥባቸው ቀናት፣ እና ምክኒያት አሳይ ችሎቶችና ሌሎችንም ያካትታል።

- <u>በተቀጠሩት ችሎቶች መቅረብ፡</u> የዲ.ቪ. ክፍል የወንጀለኛ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት፣ በከፊል በርቀት ወይም በአካል መስራቱ ይቀጥላሉ። በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ተከላካዮች ከዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) ወይም ከማህበረሰቡ (ኮሚኒቲ) እየቀረቡ በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ ይካሄዳሉ። የተከላካዮች፣ ምስክሮች፣ ተበዳዮች፣ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጁሮሮች እና ሌሎች የማህበረሰብ አባላት ጤናና ደህንነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሁሉም የፍርድ ቤት ክፍሎች በአካልና በርቀት ተሳትፎ እንዲያስችሉ ተደርገው ተዘጋጅተዋል።
  - **ተፈትተው ያሉ ተከላካዮች** እስከሚቻል ድረስ በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በአካል እንዲቀርቡ እስካላዘዘ ድረስ በቴሌፎን መቅረብ ይችላሉ።
  - ተከላካዩ በርቀት የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስት ጠበቃና የተከላካይ ጠበቃም** በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ።
  - ተከላካዩ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስት ጠበቃና የተከላካይ ጠበቃም** በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።
  - ፍርድ ቤቱ ምስክሩ በርቀት ምስክርነት መስጠት ይችላል በማለት ፍቃድ ካልሰጠ በስተቀር በሁሉም የፍርድ ቤት ሂደቶች ምስክርነታቸው የሚሰጡ **ምስክሮች** በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።
  - **የቅድመ-ክርክር አገልግሎቶች (ፕሪ-ትራያል ሰርቪስስ) እና የፍርድ ቤት**

**አገልግሎቶች እና የበዳይ ሱፐርቪዥን ኤጀንሲ ተወካዮች** በአካል መቅረብ ይችላሉ፣ ነገር ግን በርቀት በቪድዮ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን ቢቀርቡ ይበረታታሉ።

- o **የወንጀል ሰለባዎች** በአካል መቅረብ ይችላሉ፣ ነገር ግን በርቀት በቪድዮ ወይም የሚቻል ከሆነ በቴሌፎን ቢቀርቡ ይበረታታሉ።
- o **የማህበረሰብ አባላት** የይዞታ ገደብ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በአካል መቅረብ ይችላሉ፣ ነገር ግን በርቀት በቪድዮ ወይም የሚቻል ከሆነ በቴሌፎን ቢቀርቡ ይበረታታሉ።

- <u>በእስር-ያሉ የጊዜ ሰሌዳ ችሎቶች (ዲተይንድ ስኬጁሊንግ ሂሪንግስ)፡</u> በC-10 በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. ፍርድ ቤት ክፍል የተቀጠሩ በርቀት የሚካሄዱ በእስር-ያሉ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ስታተስ ሂሪንግስ) ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጣቸውም። በነዚህ የጊዜ ሰሌዳ ኮንፈረንሶች (ስኬጁሊንግ ኮንፈረንስስ) ተከላካይ መቅረብ አያስፈልግም። ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ-የሚሰማባቸው የችሎት (ሳብስታንቲቭ ሂሪንግስ) ቀን ወይም ተጨማሪ የጊዜ ሰሌዳ ችሎት ለመጠየቅ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

- <u>በእስር ያሉ ተከላካዮች፡</u> የእምነት ክህደት ቃላቸው ከሰጡ በኋላ በ C-10 የታሰሩ ተከላካዮች በ C-10 ችሎት ከቀረቡ ከሳምንት በኋላ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ችሎት (ስታተስ ሂሪንግ) ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። መዝገቦቹ በተመደበው ዳኛ ካላንደር በአካል እንዲቀርቡ ይደረጋል። የተከላካይ ጠበቃና አቃቤ ህግ ለችሎቱ በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል። በዚህ ችሎት አካላት የእስር ችሎት (ዲቴንሽን ሂሪንግ) ወይም ተጨማሪ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ቀጠሮ መጠየቅ ይችላሉ።

- <u>የእስር ችሎቶች (ዲቴንሽን ሂሪንግስ)፡</u> የመጀመሪያ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ችሎት ከተደረገ በኋላና ጥያቄ ከቀረበ የዲ.ቪ. የእስር ችሎቶች በአካል ይካሄዳሉ። ሁሉም አካላት በነዚህ ችሎቶች በአካል መገኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ችሎቶች በተመደበው ማጂስትሬት ዳኛ ይሰማሉ።

- <u>በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ)</u>፡ ዲ.ቪ.ዲ. ከዲሰምበር 2፣ 2020 ጀምሮ በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) መስማት ለመቀጠል የ30-ቀን ማስታወቂያ በኖቬምበር 2፣ 2020 አቅርቦ ነበር። በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) ፍርድ ቤቱ በሚይዘው ጉዳዩ ያለበት ደረጃ በሚታወቅበት ችሎት ቀጠሮ

ይያዝላቸዋል። ክርክሮቹ በአካል ይካሄዳሉ።

- ከእስር ለተፈቱ ተከላካዮች በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች፡ ከሰፕተምበር 7፣ 2021 ጀምሮ ዲ.ቪ.ዲ. ከእስር-ለተፈቱ ተከላካዮች በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች ዳግም ማካሄድ ጀምሯል። ክርክር የሚደረግበትና የክርክር ዝግጁነት የሚሰማባቸው ቀናት ጉዳዩ ያለበት ደረጃ በሚታወቅባቸው ችሎቶች ይወሰናል። ክርክሮቹ በአካል ይካሄዳሉ።

- የእምነት ክህደት ቃሎች (አረይንመንትስ)፡ የቤት ውስጥ ሁከት የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በፍርድ ቤት ቁጥር C-10 መሰማት ይቀጥላሉ። የሲ.ሲ.ሲ. የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ።

- ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)፡

    - በአካልና በከፊል በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል በሰኞና እሮብ እለታት ይካሄዳሉ። ተቀባይነት ያለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ተከላካዮች ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ። ተከላካይ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር የተከላካይ ጠበቃና መንግስትም በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል። ሁሉም ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።

    - ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በማንኛውም ቀን፣ ከሰኞ እስከ አርብ ሊቀጠሩ ይችላሉ። ተከላካዮች ጨምሮ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ በርቀት መቅረብ ይኖርባቸዋል።

    - በመይ 10 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ ተቀጥረው የነበሩ የፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ ችሎቶች፣ ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር በተመደበለት ቀን በርቀት በሚካሄድ የፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳሉ። ኤ.ቪ.አር. ፋይል ቢደረግ የብሮቤሽኑ ማብቂያ ያቆማል (ቶል ይደረጋል)።

- ፍርድ ቤት ሲመጡ በፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ እንዲታሰሩ የሚፈቅድ ማዘዣ (ዋክ-ኢን ቤንጅ ዋራንት) መዝገቦች፡ ከሰፕተምበር 7፣ 2021 ጀምሮ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች ከ3:30 ፒ.ኤም. በፊት ለዲ.ሲ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ፣ የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) በበኩሉ በቀኑ በተመደበው ዳኛ ፊት እንዲቀርቡ ያደርጋል።

የፍትሐ ብሔር መከላከያ ትዕዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች፣ የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) መዝገቦች፣ እና ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች፡

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)፣ በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ለማቀላጠፍ ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለመስጠት ጸሀፊ ቢሮን (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-0157 ያገኙ ዘንድ ያበረታታል። እባክዎ፣ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ይህንን የቴሌፎን ቁጥር ይደውሉ።

የፍትሐ ብሔር መከላከያ ትዕዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች፡

- ፋይል የተደረገው በአካልም ይሁን በርቀት፣ የጊዝያዊ መከላከያ ትዕዛዞች ጥያቄዎች በርቀት በዳኛ መሰማት ይቀጥላሉ። ከመይ 10፣ 2021 ጀምረው የተጠየቁ አዳዲስ የቲ.ፒ.ኦ. ጥያቄዎች ፋይል ከተደረጉበት በኋላ ባሉ 2 ወይ 3 ሳምንታት በኋላ አገልግሎታቸው ያበቃል። እባክዎን፣ ከመይ 10፣ 2021 በፊት የተላለፉ ቲ.ፒ.ኦ.ዎች፣ ጉዳዩ ፋይል በተደረገበት ቀን መሰረት ጉዳዩ ባየው ዳኛ አስቀድሞ ባስቀመጠው የመርሀግብር ትእዛዞች መሰረት በመጪው ጊዜ አገልግሎታቸው ያበቃል።

- የቲ.ፒ.ኦ. ጥያቄዎች በርቀት በሚካሄድ ፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ። የቲ.ፒ.ኦ. ጥያቄ ፋይል ከተደረገ በኋላ የዲ.ሲ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) ለችሎቱ አስፈላጊ የሚባሉትን መረጃዎች ለአቤቱታ አቅራቢ ያቀርባሉ። ፋይል አድራጊዎች በርቀት ለመከታተል የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመጻፍ ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፣ የፍርድ ቤቱ የቴሌፎን ጥሪ ለመቀበልም ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል። በአካል ፋይል የሚያደርጉ ፋይል አድራጊዎች የጸሀፊ ቢሮ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት በአካል ወደሚደረግ ችሎት ይቀርባሉ።

- አካላቱ ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በሰው በኩል የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

- ሁሉም የሲ.ፒ.ኦ፣ ኤ.ኤስ.ኦ.፣ ኤ.አር.ፒ.ኦ. እና ተመሳሳይ መዝገቦች ጉዳዩ ፋይል ከተደረገ በኋላ ከሁለት ሳምንታት አከባቢ ይካሄዳሉ።

<u>አንድ አካል ብቻ ባለበት የተወሰኑ የሲ.ፒ.ኦ. መዝገቦች (ዲፎልት ሲ.ፒ.ኦ. ኬዝስ) የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣዎች (ቤንች ዋራንትስ)</u>: የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው መልስ ሰጭዎች (ሪስፖንደንትስ) በዛኑ ቀን በአካል ዳኛ ፊት ይቀርቡ ዘንድ በዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በ3:30 ፒ.ኤም. ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ።

<u>በሲ.ፒ.ኦ. ምክኒያት የተነሱ የልጅ ቀለብ (ቻይልድ ሳፖርት) መዝገቦች</u>

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) ወደ ክፍሉ የተመደቡ የልጅ ቀለብ መዝገቦች በምናባዊ የፍርድ ቤት ክፍል (ቨርቹዋል ኮርትሩም) ይሰማል። ተከራካሪ ወገኖች ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።

<u>የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) መዝገቦች (ኤ.ኤስ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች፡</u>

- ፋይል የተደረገው በአካልም ይሁን በርቀት፣ የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) (ኤ.ኤስ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች በርቀት በሚሰራ ዳኛ መስማት ይቀጥላል። ዳኛው ኤ.ኤስ.ኦ.ውን በርቀት በተካሄደ ችሎት ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካላራዘመ በስተቀር ሁሉም የኤ.ኤስ.ኦ. የሚያበቁባቸው ቀናት ጉዳዩ ፋይል በተደረገበት ቀን መሰረት ጉዳዩን እያየ ባለው ዳኛ በሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ትዕዛዝ መሰረት መሆን ይኖርባቸዋል።
    - <u>የታ.ሶ. ችሎቶች</u>: ታሶ ይሰጥ ዘንድ የሚደረጉ ጥያቄዎች በርቀት በሚካሄድ የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ። የታሶ ጥያቄ አንዴ ፋይል ከተደረገ በኋላ የዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) ለችሎቱ አስፈላጊ የሚባሉትን መረጃዎች ለአቤቱታ አቅራቢ ያቀርባሉ። ፋይል አድራጊዎች በርቀት ለመከታተል የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመጻፍ ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፣ የፍርድ ቤቱ የቴሌፎን ጥሪ

ለመቀበልም ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል። በአካል ፋይል የሚያደርጉ ፋይል አድራጊዎች በርቀት የሚካሄደውን የፍርድ ቤት ክፍል በዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ እርዳታ ከፍርድ ቤቱ ሆነው መከታተል ይችላሉ።

- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ኤ.ኤስ.ኦ.ዎችና ሌላ ከመዝገብ-ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በራስ መንገድ ሰነዶቹን ለተከላካይ ማድረሻ ሰነዶች) በኢሜይል ጨምሮ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በኩል ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች ጥያቄዎች፡

- የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና የመጨረሻ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ ጥያቄዎች መደረግ ይችላሉ፣ እና በስራ ሰአታት በአካል በጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ)፣ ወይም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ወደ DVD@dcsc.gov ኢሜይል በማድረግም ፋይል መደረግ ይችላሉ። ማመልከቻው ከዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች ድረገጽ DC Courts website ማግኘት ይቻላል። የተመደበው ዳኛ ጉዳዩን በርቀት የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማዋል።

- ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር ሁሉም *የኤክስ ፓርተ* (አንድ አካል ብቻ) ኢ.አር.ፒ.ኦ. የሚያከትሙባቸው ቀናት ጉዳዩን እያየ ባለው የዲ.ቪ.ዲ. ዳኛ በጃንዋሪ 18፣ 2021፣ ወይም ማርች 31፣ 2021 በሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ትዕዛዝ መሰረት ይራዘማሉ።

- እንዲራዘም የሚጠይቅ ማመልከቻ ፋይል ካልተደረገ በስተቀር ሁሉም በተግባር ላይ ያሉ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች በትዕዛዙ በሰፈረው ማከተሚያ ጊዜ ተግባራዊነታቸው ያበቃል።

- ክፍሉ ከኖቬምበር 9፣ 2020 ጀምሮ በከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዝ (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደር) ቀጠሮ ተይዞላቸው የነበረ መዝገቦች መስማት ጀምሯል። ሁሉም ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች ክርክሮችና ከኢ.አር.ፒ.ኦ.-ተዛማጅነት ያለቸው አቤቱታዎች በዲ.ቪ.ዲ. ጉዳዩን እያየ ባለው ዳኛ በጃንዋሪ 18፣ 2021፣ ወይም ማርች 31፣ 2021 በሰጠው የሲ.ፒ.ኦ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. የጊዜ ሰሌዳ ትዕዛዝ በተቀመጠው ቀን ይካሄዳሉ። አዲሱ የአገልግሎት ማብቂያ ጉዳዩ ፋይል የተደረገበት **የመጀመሪያው ቀን** መሰረት ያደረገ ይሆናል። ማንኛውም በኤፕሪል 1፣ 2021 እና መይ 9፣ 2021 መካከል የተሰጠ የአንድ አካል ብቻ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች በማርች 30፣ 2021 በፕሪሳይዲንግ ዳኛ ባስተላለፈው የቀነ ቀጠሮ ትእዛዝ (ስኬጁሊንግ ኦርደር) በተቀመጠው ቀን አገልጉሎቱ ያበቃል። ማንኛውም ከመይ 10፣ 2021 በኋላ የተሰጡ የአንድ አካል ብቻ

ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች ፋይል ከተደረጉበት ከሁለት ሳምንታት ገደማ በኋላ ወይም በ የአንድ አካል ብቻ ኢ.አር.ፒ.ኦ. በተጻፈው ቀን አገልግሎታቸው ያበቃል።

- ተከራካሪ ወገኖች ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።
- ተከራካሪ ወገኖች የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና ሌሎች ከመዝገብ-ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች በኢመይል ጨምሮ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በኩል ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

<u>**የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)**</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም፣ <u>ይህ የማይሆነው በሚከተሉት ነው፡</u>

1. <u>የበደል እና ቸልተኝነት (አቢዩዝ ኤንድ ኒግለክት) መዝገቦች፣ እና ተያያዥ መዝገቦች፡</u>

በቸልተኝነት መዝገቦች፣ የጉዲፈቻ መዝገቦች፣ የወላጅነት መብቶች ማቆሚያ (ተርሚኔሽን ኦፍ ፓረንታል ራይትስ) መዝገቦች፣ እና የሞግዚትነት መዝገቦች ያሉ የማመልከቻዎች ልምድና ግኝት (ሞሽንስ ፕራክቲስ ኤንድ ዲስካቨሪ)፣ በተመደበው ዳኛ ካልታዘዘ በስተቀር በሱፐርየር ፍርድ ቤት ተገቢ ደንቦች መመራቱ መቀጠል ይኖርባቸዋል። ጉዲፈቻዎችና የሴፍ ፋሚሊ ህግ (ኤ.ኤስ.ኤፍ.ኤ.) የጊዜ ገደቦች ተግባር ላይ መዋልን ይቀጥላሉ።

የጉዲፈቻ አቤቱታዎች (አዳፕሽን ፐቲሽንስ) በ https://dcscgov.app.box.com/f/aeaf4eb2153743519a495d3f95d26c93 በሚገኘው የዲጂታል መጣያ ሳጥን (ዲጂታል ድሮፕ ባክስ) በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ሁሉም ሌሎች በጉዲፈቻ መዝገቦች የሚደረጉ ልውውጦች በርቀት በኢ-ፋይሊንግ/ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

2. <u>የቤት ውስጥ ግንኙነት መዝገቦች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ ኬዝስ)፡</u>

በተመደበው ዳኛ ካልታዘዙ በስተቀር፣ ጠበቆችና ተከራካሪ ወገኖች ማመልከቻዎችና ተቃውሞዎች ፋይል ማድረግን ጨምሮ የሚመለከታቸው የስርዓት ደንቦችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም በማርች 20፣ 2020 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ በተሰጡ ትዕዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ። ሁሉም ከማርች 20፣ 2020 በፊት በተሰጡ ትዕዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች በ90 ቀናት ተራዝመዋል። ከውሳኔ በኋላ ለሚደረጉ አቤቱታዎች (ፖስት ጃጅመንት ሞሽንስ) ሰነዶች ማድረሻ ማረጋገጫ (ፕሩፍ ኦፍ ሰርቪስ) በ60 ቀናት ውስጥ ፋይል አለማድረግ ጸሀፊ መዝገቡ እንደገና መከፈት በሚችልበት ሁኔታ (ዊዝ አዉት ፕረጁዲዝ) እንዲሰረዝ ሊያስደርግ ይችላል።

ግለሰቦች ማህበራዊ ርቀትንና መጥሪያ ማድረስ (በአካልም ይሁን ሰርቲፋይድ ፖስታ ለማግኘት ወደ ፖስታ ቤት በመሄድ) "በቅንነት የሚደረግ ሙከራ (ዲሊጀንት ኤፈርትስ)" የማድረጋቸው እድል የመነመነ ስለሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስኪያስተላልፍ ድረስ፣ በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በጽሁፍ መልእክት (ቴክስት መሰጅ) ወይም በኢመይል በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ሰነዶችና መጥሪያ ማድረስ ይፈቀዳል። መጥሪያው የሚያደርስ አካል ለተመደበው ዳኛ በሚያረካ መንገድ ማድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ የተፈጸመው የማድረስ ዘዴ "ትክክለኛውን ማስታወቂያ ለመስጠት በምክንያታዊነት የተሰላ" መሆኑ የሚያሳይ መሆንን ያካትታል። በአካል ማድረስ በህግ፣ በዲ.ሲ. ኮድ §§ 13-332 (አቅመ አዳም ያልደረሱትን በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ 13-333 (ብቁ ላልሆኑ (ኢንኮፐተንት) ሰዎች በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ እና 46-206 (ድጋፍ (ሳፖርት) የተመለከቱ መዝገቦች በአካል ማድረስ ያስገድዳል) ጭምር፣ የተደነገገ ከሆነ ተከራካሪ ወገኖች በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማድረስ አይችሉም።

በሲፒርየር ፍርድ ቤት የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ደንብ 5(d)(5)(B) መሰረት ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ቤት ሰነዶች ማድረሻ ቃለ መሀላ (አፊዳፊት ኦፍ ሰርቪስ ፕሮሰስ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል እንዲያደርጉ ይፈቅዳል።

3. <u>የአእምሮ ተሀድሶ (ሜንታል ሀቢሊቴሽን) መዝገቦች፡</u>

በአስተዳደር ትዕዛዝ ቁጥር 00-06 መሰረት የመልስ ሰጭዎች ጠበቆች የአሁናዊ ሁኔታ ሪፖርቶች ፋይል ማድረጉን መቀጠል ይኖርባቸዋል፣ እስከሚቻል ድረስም የመልስ ሰጭዎች መረጃ መሰረት ያደረገ በፈቃደኝነት የሚደረግ ቁርጠኝነት ፈቃድ ሪፖርት (ሪስፖንደንትስ ሪፖርትስ ኦን ኢንፎርምድ ኮንሰንት ፎር ቮሉንታሪ ኮሚትመንት) እና የተተኪ ውሳኔ ሰጭ

ሪፖርቶች (ሳብስቲቱት ደሲሽን ሜከር ሪፖርትስ) ፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል። ተከራካሪ ወገኖች ልዩ ሪፖርት ወይም የተወሰነ ሰነድ ፋይል እንዲያደርጉ የሚያዝ ትዕዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል። ተከራካሪ ወገኖች ማንኛውንም ነባር ትዕዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል (a) ተሳታፊዎች ስብሰባ እንዲያደርጉ የሚያዝ ወይም (b) ወረርሽኙ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በሚቻል መጠን ዲፓርትመንት ኦፍ ዲስኤቢሊቲ ሰርቪስስ (የአካል ጉዳተኞች ክፍል) የተወሰኑ አገልግሎቶች ወይም ድጋፍ እንዲያቀርብ የሚያዝ ትዕዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል።

**የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት በአካል የሚካሄዱ የችሎቶች አይነቶችን ያካሂዳል፡**

በሀላፊነት አለመወጣት (ዴሊኩዌንሲ) መዝገቦች እውነታ ለማወቅ የሚደረጉ ችሎቶች— ቅድሚያ የሚሰጣቸው በከፍተኛ እስር (ሰኪዩርሊ ዲተይንድ) ላሉ መልስ ሰጭዎች ሲሆን፣ በመቀጠልም በመጠለያ ቤቶች ላሉ መልስ ሰጭዎች ቅድሚያ ይሰጣል። ጥሩ ምክኒያት ከቀረበና የቤተሰብ ፍርድ ቤት ዋና ዳኛ ወይም ምክትል ዋና ዳኛ ካጸደቀ፣ ሌሎች የመዝገብ አይነቶች በአካል ሊደረጉ ይችላሉ። በአካል የሚደረጉ ችሎቶች በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር JM-12 እና ከተገኘም በሌሎች የፍርድ ቤት ክፍሎች ይካሄዳሉ። ክርክሩን የሚሰማው ዳኛ እነዚህን ችሎቶች በተመለከተ ሊነሱ ስለሚችሉ ማናቸውንም የሚያሳስቡ ነገሮች በቅድመ-ክርክር ችሎት ይፈታቸዋል።

**የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት የችሎቶች አይነቶችን በርቀት በማካሄድ ይገኛል፡**

<u>የበደል እና ቸልተኝነት መዝገቦች፣ ተያያዥ መዝገቦች:</u>

- የቸልተኝነት የመጀመሪያ ችሎቶች (ነግለክት ኢኒሻል ሂሪንግስ)
- አስቸኳይ ችሎቶች (ኢመርጀንሲ ሂሪንግስ)
- የክስ ማጠናቀቂያ (ዲስፖዚሽን) ችሎቶች
- የስምምነት ችሎቶች (ስቲፑሌሽን ሂሪንግስ)
- *ቲ.ኤ. ኤል. (Ta. L.)* ችሎቶች፣ ጉዲፈቻዎች፣ የወላጅነት መብቶች ማቆሚያ ማመልከቻዎች፣ እና የሞግዚትነት ክርክሮች ጨምሮ ማናቸውም አይነት ክርክሮች።
- የቤተሰብ እንክብካቤ ፍርድ ቤት ችሎቶች
- የቋሚነት ችሎቶች (ፐርማነንሲ ሂሪንግስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያ ምዘና (ረቪው ኦፍ ዲስፖዚሽን) ችሎቶች፣ እና የቅድመ-ክርክር ችሎቶች ቀነ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል
- ሌሎች ችሎቶች።

<u>የቤት ውስጥ ግንኙነቶች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ)፡</u>

- ፍቺ፣ የጋብቻ ሽረት፣ ህጋዊ መለያየቶች፣ የኮሞን ሎው ጋብቻ፣ ባለአደራነት፣ የልጅ ቀለብ፣ እና ሌሎች ፍርድ ቤቱ ተገቢ ናቸው የሚላቸው እንደነዚህ አይነት ጉዳዮች ያካተቱ ክርክሮች እና ችሎቶች።
- የቤት ውስጥ ግንኙነት በዛኑ ቀን የሚካሄዱ አስቸኳይ ችሎቶች (ሴም ደይ ኢመርጀንሲ ሂሪንግስ)።
- ባለአደራነት ለማሻሻል የተደረጉትን ወይም በዛኑ ቀን እንዲደረጉ አስቸኳይ ችሎት ተጠይቆ የተከለከለበት የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ኮንተምፕት) አስቸኳይ አቤቱታዎች፣ ነገር ግን አቤቱታውን ባፋጣኝ መስማቱ አስፈላጊና የሚቻል መሆኑ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ ላይ የደረሰ ከሆነ።

<u>የወጣት ጥፋተኛ ሀላፊነት አለመወጣት (ጁቨናይል ደሊኩዌንሲ)፣ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሰዎች፣ እና የግል ጉዲፈቻዎች፡</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ ሁሉም የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በተግባር ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ፣ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም። ይህ ትዕዛዝ ቢኖርም፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ያከናውናል፡

- ምክኒያታዊ ጥርጣሬ ችሎቶች (ፕሮባብል ከውዝ ሂሪንግስ) ጨምሮ የወጣት ጥፋተኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ጁቨናይል ኢኒሻል ሂሪንግስ)።

- ዳኛው ችሎቱን ማካሄድ ጉዳዩን ለመፍታት ጠቃሚ ነው፣ ወይም የጥፋተኛ ወጣቱ የእስር ጊዜ ሊቀይር ይችላል፣ ብሎ በማመን ከወሰነ፣ ማናቸውም ሌሎች ችሎቶች (ለምሳሌ፣ አስቸኳይ ችሎቶች፣ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያ ችሎቶች (ዲስፖዚሽን ሂሪንግስ)) ሊደረጉ ይችላሉ፣ ይህ የሚመለከተው ለሆፕ (HOPE) እና ወጣት ጥፋተኛ የጠባይ አቅጣጫ መለወጥ (ጁቨናይል ቢሀቭዮራል ዳይቨርሽን) ፕሮግራም (ጀይ.ቢ.ዲ.ፒ.) የፍርድ ቤት ክፍሎች ነው።

- በወጣት ጥፋተኞች መዝገቦች እውነታ ለማወቅ የሚደረጉ ችሎቶች በአካል (ከላይ ያለውን የቤተሰብ ፍርድ ቤት በአካል-የሚካሄዱ ክርክሮች የሚል ሴክሽን ይመልከቱ)

ሊካሄዱ ይችላሉ። እውነታ ለማወቅ የሚደረጉ ችሎቶች በርቀት ሊካሄዱ የሚችሉት ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ እውነታ ለማወቅ የሚደረገውን ችሎት ለፍትህ ጥቅም ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርስ ተጨማሪ ሊራዘም አይችልም የሚያስብል የተወሰኑ ምክኒያቶች የደረሰበት ከሆነ ብቻ፣ እና ከጠበቃ ጋር ከተመካከረ በኋላ በመልስ ሰጭው ፈቃድ የሚካሄዱ ናቸው።

- ልዩ ስደተኛ ወጣት ጥፋተኛ (ስፔሻል ኢሚግራንት ጁቨናይል) ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)።

- የግል ጉዲፈቻዎች (ፕራይቬት አዳፕሽንስ)።

<u>የአእምሮ ጤና (ሜንታል ሄልዝ)</u>፡

- የአእምሮ ጤና ምክኒያታዊ ጥርጣሬ ችሎቶች (ፕሮባብል ከውዝ ሂሪንግስ)።
- የአእምሮ ጤና ኮሚሽን ችሎቶች።
  የስረዛ ችሎቶች (ሪቮኬሽን ሂሪንግስ)፣ በሚያስፈልጉበት ጊዜ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ አስቸኳይ ችሎቶች፣ ቅድመ-ክርክር ችሎቶች፣ እና ክርክሮች (ትራያልስ)።

<u>የአእምሮ ማገልመሻ (ሜንታል ሀቢሊቴሽን):</u>

- የአእምሮ ማገልመሻ ምዘና፣ እና አስቸኳይ ችሎቶች።

<u>የስም ለውጦች:</u>

- የስም ለውጥ ችሎቶች ይካሄዳሉ።

<u>የወላጅነትና የድጋፍ (ፓረንቴጅ ኤንድ ሳፖርት) መዝገቦች:</u>

- ሁሉም ቀነ ቀጠሮ እየተሰጣቸውና፣ የሚቻል ከሆነም በወረቀት በመፍታት ይገኛል።

<u>ሌላ ተዛማጅነት ያለው መረጃ:</u>

አሁንም ቢሆን በርቀት ፋይል ማድረግ ይቻላል፣ ነገር ግን ውሱን አገልግሎቶችን በፍርድ ቤቱ በአካል ማድረግ ይቻላል (ከታች ያለው 'በአካል ሊደረጉ የሚችሉ አገልግሎቶች' የሚለውን ክፍል

ይመልከቱ)።

- የቤት ውስጥ ግንኙነቶች አስቸኳይ አቤቱታዎች ፋይል ማድረጊያ ሂደት፡
    - በጠበቃ የተወከሉ ተከራካሪ ወገኖች ማናቸውም አስቸኳይ አቤቱታዎችን በ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በመጠቀም ኢፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል።
        - ተከራካሪ ወገኖች "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - 501(c)(3) በሆኑ ድርጅቶች የተወከሉ ተከራካሪዎች እና ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪዎች አስቸኳይ አቤቱታዎችን በ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በመጠቀም ኢፋይል ማድረግ ይችላሉ።
        - ተከራካሪ ወገኖች "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - ራሳቸውን የወከሉ፣ ከፋይል ማድረግያ ክፍያ ነጻ የተባሉ እና ኢፋይል ማድረግ ያልፈለጉ ተከራካሪዎች አቤቱታውን ወደ ኢመይል FamilyCourtClC@DCSC.GOV አያይዘው መላክ ይችላሉ። ፋይል አድራጊዎች በእንደዚህ ኢመይሎች ሳብጀክት መስመር (Subject Line) "አስቸኳይ አቤቱታ (Emergency Motion)" ብለው መጻፍ ይኖርባቸዋል። ራሳቸውን የወከሉ፣ ከፋይል ማድረግያ ክፍያ ነጻ ለመባል ለመጀመሪያ ጊዜ እየጠየቁ ያሉ ተከራካሪዎች ጥያቄያቸውና አስቸኳይ አቤቱታውን ወደ FamilyCourtClC@DCSC.GOV መላክና፣ በሳብጀክት መስመር (Subject Line) "አስቸኳይ አቤቱታና ከክፍያ ነጻ እባል ዘንድ እጠይቃለሁ (Emergency Motion and Fee Waiver Request)" ብለው መጻፍ ይኖርባቸዋል።
        - ራሳቸውን የወከሉና ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በመጠቀም ኢፋይል እያደረጉ ያሉ ተከራካሪዎች "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - ራሳቸውን የወከሉ፣ ከፋይል ማድረግያ ክፍያ ነጻ ያልተባሉ ተከራካሪዎች አስቸኳይ አቤቱታዎችን በ https://www.dccourts.gov/superior-court/efiling በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በመጠቀም ኢፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል።

        - ተከራካሪ ወገኖች "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - ፋይል አድራጊ አቤቱታውን ከላይ እንደተጠቀሰው አስቸኳይ መሆኑ በስነ ስርአት ካልለየ አቤቱታው በጊዜ ሂደት ላይደረግለት ይችላል።

- በቤተሰብ ፍርድ ቤት የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች ፋይል የሚደረግበት ሂደት በፍርድ ቤቱ ድረገጽ በዝርዝር ይገኛል፣ [https://www.dccourts.gov/sites/default/files/DRB-Case-InitiationInstructions-for-filers.pdf](https://www.dccourts.gov/sites/default/files/DRB-Case-InitiationInstructions-for-filers.pdf) ይመልከቱ።

- የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ-ሄልፐ ሰንተር) (202-879-0096) በቤተሰብ ፍርድ ቤት መዝገቦች (ፍቺ፣ የልጅ ባለአደራነት (ቻይልድ ካስተዲ)፣ የልጅ ቀለብ፣ ወዘተ) መረጃ ለመስጠትና ተከራካሪ ወገኖች ሰነዶች ፋይል ማድረግ እንዲችሉ ለመርዳት በርቀት ይሰራል።

- ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤት መጥሪያዎች በኢሌክትሮኒካዊ መንገድ ይሰጣል፣ ፋይል ወዳደረገ አካልም በኢመይል ይልካል።

- ክትትል የሚደረግበት የጉብኝት ማእከል (ሱፐርቫይዝድ ቪዚቴሽን ሰንተር) የመግቢያ ቃለ ምልልሶችና (ኢንቴክ ኢንተርቪውስ) ክትትል የሚደረግባቸው ጉብኝቶች በርቀት በማካሄድ ላይ ይገኛል።

- ባለ ብዙ-በር (መልቲ-ዶር) ሽምግልና እና የሽምግልና ምዝገባ በቪድዮኮንፈረንስ ወይም በቴሌፎን መሳተፍ ለሚችሉ ተከራካሪ ወገኖች በርቀት መደረግ ይችላል።

- የፓክ (በባለአደራነት መዝገቦች የስምምነትና መተጋገዝ ፕሮግራም) አብሮ አስተዳደግ (ኮ-ፓረንቲንግ) ሴሚናሮች በወር ሁለት ጊዜ እንደገና ተጀምረዋል።

<u>በአካል የሚሰጡ አገልግሎቶች:</u>

የቤተሰብ ፍርድ ቤት የህዝብ ጽህፈት ቤቶች (ማእከላዊ መቀበያ ማእከል (ሰንትራል ኢንቴክ) ሰንተር፣ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች፣ ወላጅነትና ድጋፍ፣ የወጣት ጥፋተኛ (ጁቨናይል) እና ቸልተኝነት፣ የአእምሮ ጤና እና ተሀድሶ፣ የልጅ ጉዳትና ቸልተኝነት ምክር፣ እና የጋብቻ ቢሮ

ያጠቃለለ) በአካል አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ይሆናሉ። የቤተሰብ ፍርድ ቤት በተጨማሪ በኢፋይሊንግ በኩል የተላኩ ሰነዶችን ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ መዝገቦች ለምዘና ወደ ዳኛ ይላካሉ፣ እና አብዛኛዎቹ ችሎቶች በርቀት ይካሄዳሉ። እባክዎን፣ ሁሉም የአስቸኳይ መዝገቦች ከአመት በአሎች በስተቀር ከሰኞ እስከ አርብ ከ4፡00 ፒ.ኤም. በፊት ፋይል መደረግ እንደሚኖርባቸው ልብ ይበሉ።

ጠበቆችና ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪ ወገኖች ሰነዶችን በ https://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝፋይልኤክስፐረስ በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

የባለአደራነት፣ የፍቺ እና/ወይም የልጅ ቀለብ ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና ፋይል በማድረግ ረገድ እርዳታ ለሚፈልጉ ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪ ወገኖች የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) በ 202-879-0096 ማግኘት ይኖርባቸዋል።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎል ወይም የሰነዶች ቅጂ ቢፈልጉ እባክዎን የቤተሰብ ፍርድ ቤት የጥሪ ማእከልን (ፋሚሊ ኮርት ኮል ሰንተር) በ202-879-1212 በመደወል ወይም ወደ FamilyCourtCertifiedCopies@dcsc.gov ኢመይል በመላክ ያግኙዋቸው።

## የጋብቻ ቢሮ (መርየጅ ቢሮ)

የጋብቻ ቢሮ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎች በአካልና በርቀት ሂደት በማድረግ ላይ ይገኛል፣ የጋብቻ ስነ ስርአቶችም በቪድዮኮንፈረንስ እያደረገ ይገኛል። ሁሉም አካላት- ተጋቢዎቹና የጋብቻ ስነ ስርአቱ የሚመራ ሰው- ስነ ስርአቱ በሚፈጸምበት ሰአት በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በአካል ሊኖሩ ይገባል።

የማመልከቻ ሂደቱ ለመጀመር እባክዎን በhttps://www.dccourts.gov/form/marriage-application የሚገኘውን ማመልከቻ በማጠናቀቅ ያስረክቡ። ማመልከቻውን ለማጠናቀቅና ለማስረከብ ኮምፒውተር ወይም ሞባይል መሳሪያ (አይፓድ፣ ታብሌት፣ ወይም ስማርት ቴሌፎን) መጠቀም ይችላሉ። በመቀጠል የጋብቻ ቢሮ ተወካይ የማመልከቻ ሂደቱን ያጠናቅቁ ዘንድ ያገኝዎታል። ምንም እንኳን የጋብቻ ምስክር ወረቀትዎ በአካል መጥተው የሚወስዱት ቢሆንም ማመልከቻዎ በበይነ መረብ (ኦንላይ) ያደርጉ ዘንድ ይበረታታሉ።

በኦንላይን ማመልከት ካልቻሉ፣ ማመልከቻውን በአካል ማጠናቀቅ ይችላሉ።

**<u>የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች</u>**

በግብር (ታክስ)፣ እና በኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች የነበረ እግድ አሁን ተነስቷል፣ እና በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ባሁኑ ሰአት በሙሉ ሀይል ተግባር ላይ ይውላሉ።

በአካል የሚደረጉ አገልግሎቶች፡

- የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች የህዝብ አገልግሎት ባንኮዎች (ካውንተሮች) ሰነዶችን በአካል ፋይል ማድረግ ለሚፈልጉ ወይም መዝገቦችን በአካል ማየት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚፈልጉትን ያደርጉ ዘንድ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5:00 ፒ.ኤም. ክፍት ናቸው።

በርቀት የሚደረጉ አገልግሎቶች፡

- አገልግሎቶች በርቀት መሰጠት ይቀጥላሉ፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግም ይቀጥላል። ሁሉም ተቀጥረው ያሉ ችሎቶች በርቀት ይካሂዳሉ። በአካል እንዲቀርቡ በዳኛው ካልታዘዙ በስተቀር ማናቸውም ተከራካሪ ተከራካሪ ወገኖች ወይም ጠበቆች በአካል መቅረብ የለባቸውም።
- የኑዛዜ ማረጋገጫ ራስ-አግዝ ማእከል (ፕሮቤት ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) (ProbateSelfHelpCenter@dcsc.gov) የጣልቃ ገብነት ሂደቶችና (ኢንተርቬንሽን ፕሮሲዲንግስ) አነስተኛ ርስት በተመለከተ ፋይል የሚደረጉ ነገሮች (ስሞል ኢስቴት ፋይሊንግስ) ፋይል በማድረግ ዘንድ መረጃና እርዳታ ለመስጠት በርቀት በመስራት ላይ ይገኛል።

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ዳኞች የሚከተሉትን መዝገቦች በርቀት በዌብኤክስ ይሰማሉ፡
    - የ21-ቀን አስቸኳይ ሞግዚቶች (ኢመርጀንሲ ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ፣ ወይም በአካል ፋይል የተደረጉ።

- ○ የ90-ቀን የጤና-ጥበቃ ሞግዚቶች (ሄልዝ-ኬር ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ፣ ወይም በአካል ፋይል የተደረጉ።

- ○ የአጠቃላይ የፍርድ ቤት ሂደት ማመልከቻዎች (ፐቲሽንስ ፎር ጀነራል ፕሮሲዲንግስ) (የሞግዚትነት እና ተንከባካቢነት ማመልከቻዎች (ጋርድያን ኤንድ ኮንዘርቫቶርሺፕ ፐቲሽንስ)) – በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) እና በፖስታ (ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ፣ ወይም በአካል።

- ○ ዳኛው ዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው ሌሎች የጣልቃገብነት መዝገቦች (ኢንተርቬንሽን ማተርስ)

- ○ ዳኛው በዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው የንብረት መዝገቦች (ኢስቴት ኬዝስ) ጨምሮ፣ ሌሎች የኑዛዜ ማረጋገጫ መዝገቦች

- በርቀት ለሚካሄዱ ችሎቶች፣ የአዳዲስ መዝገቦች ፋይል ማድረጎች እና የፍርድ ቤት ትእዛዞችና የክፍል ማስታወቂያዎች መድረስ ለማቀላጠፍ የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ፋይል ስለ ተደረጉ መዝገቦች በተመለከተ፣ እንደነ ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ፣ የመገኛ መረጃዎች እንዲያቀርቡ ያበረታታል።

- የሞግዚትነት ቀጠሮዎች ሶስት ዓመታዊ ግምገማዎች በጃንዋሪ 2፣ 2022 መካሄድ ይቀጥላሉ።

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) አገልግሎቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ቢፈልጉ እባክዎን የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) አሰራሮች ማስታወቂያ ይመልከቱ። https://www.dccourts.gov/superior-court/probate-division

የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) እና ጉዳዩ ያለበት ሁኔታ (ስታተስ ሂሪንግ) ችሎቶች፣ ከየመጀመሪያ የመርሀግብር (ኢኒሻል ስኬጁሊንግ) እና ቅድመ-ክርክር ኮንፈረንሶች በተጨማሪ በርቀት በዌብኤክስ በመጠቀም ይካሄዳሉ።

- ሽምግልናዎች በርቀት በ Zoom.gov ይካሄዳሉ።

- በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶችና ሽምግልናዎች ለማቀላጠፍ፣ በሁሉም ፋይል የሚደረጉ ሰነዶች ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢሜይል አድራሻዎች የመሳሰሉ፣ የመገኛ መረጃዎች እንዲያቀርቡ የግብር ክፍል ያበረታታል።

- ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪ ወገኖች ፋይል ለሚያደርጓቸው ማመልከቻዎች (ፕሊዲንግስ) ወይም የማመልከቻዎቹ ምስል ወደ TaxDocket@dcsc.gov በኢሜይል መላክና ፋይል ማድረጊያ ክፍያ በቼክ ወይም ማኒ ኦርደር ወደ D.C. Superior Court, Tax Division, 500 Indiana Ave., NW, Suite 4100, Washington, DC 20001 መላክን መቀጠል ይችላሉ።

**<u>የኦዲተር ማስተር ቢሮ</u>**

ኦዲተር ማስተሩ ሁሉንም ችሎቶች በርቀት በዌብኤክስ በኩል እያካሄደ ነው። ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎን ወይም በቪድዮ-ኮንፈረንስ መሳተፍ ይችላሉ። በርቀት እንዴት መሳተፍ እንዳለብዎ የሚያሳዩ መመሪያዎች ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ይሰጣሉ።

ኦዲተር ማስተሩ ከኦገስት 1፣ 2020 ጀምሮ ያስተላለፋቸውን ሁሉም ትዕዛዞች ተከራካሪ ወገኖች ማክበር ይኖርባቸዋል። ቢሮው ባሁኑ ሰአት አስቀድመው ተቀጥረው የነበሩ የሁሉንም ችሎቶች ሌላ ቀነ ቀጠሮ የሚሰጥ ትዕዛዝ፣ በአዳዲስ መዝገቦች የችሎቶች ቀነ ቀጠሮ፣ እና ሰነዶች የሚቀርቡባቸው አዳዲስ ቀናት የያዙ የተለያዩ ትዕዛዞችን በመስጠት ይገኛል።

ሰራተኞች (ስታፍ) በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5:00 ፒ.ኤም. ከሰኞ እስከ አርብ ይገኛሉ። ሰራተኞች ሁሉንም ሰነዶች በርቀት ሂደት እያደረጉ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ሰነዶች በኢሜይል ለAuditor.Master@dcsc.gov ወይም በፖስታ ለ፡ Office of the Auditor-Master, 500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። በሚስጢር መያዝ የሚኖርባቸው (ሰንሲቲቭ ኢን ኔቸር) ሰነዶች በኢሜይል በኩል ወደ AMFinancialBox@dcsc.gov መላክ ይቻላል።

ሁሉም ችሎቶች የተደረጉባቸውና ሁሉም ሰነዶች የተረከቡባቸው መዝገቦች በተመለከተ ሪፖርቶች በመዘጋጀት ይገኛሉ። ሪፖርቶች እንደተጠናቀቁ ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርሱ ይደረጋሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎ ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ወይም በኢሜይል

በAuditor.Master@dcsc.gov ያግኙ።